# ወጋየሁ ደግነቱ

ሰጎን[1]ኦልኬስትራን አቅንቶ ያቆመው
የወበራው ጀግና ወጋየሁ ደግነቱ ነው።
በልጅነት ወራት የማንጎራጉረው
“እናትና አባቴን በተለየኋቸው”
ትዝ ይለኛል ዛሬም ግጥሙ ከነዜማው።
አመት አዲስ አመት በመጣ ቁጥር
አንበሳና ስጎን ሁሌ ፍክክር
አሸናፊ የሌለው ያመት ውድድር
ይተባል ይገናል ጊዜው ሲጨምር።

መስፍንና ሲሳይ ካንበሳው ክ/ጦር
ወጋየሁ መርአዊ ከምስራቃዊ ሰጎን
ነበሩ ከዋክብት ከምስራቁ ወገን።

ክንፈ ሚካኤል እንደ ሞከረው ተረጎመው
ሐምሌ ፲፫ ቀን ፳፻፩ ዓ/ም
ሜልንበርን፣ አውስትራሊያ

---

[1] የሐረር ፓሊስ ምስራቃዊ ሰጎን የወታደሩ አንበሳው ክ/ጦር ኦልኬስትራ ይባል ነበር